# የDCPS ተማሪ እና ሠራተኛ በቴክኖሎጂና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ የመጠቀሚያ ፖሊሲ

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ለተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ የኢንተርኔት፣ የመረጃ ስብስብ (data) እና የኔትወርክ ዘዴዎችን (DCPS network) እንዲያገኙ ያደርጋል። DCPS በተጨማሪም ለተማሪዎች የኮምፒውተሮች፣ የታብሌቶች፣ ዲቫይሶች፣ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንደ ፐሪንተሮች (printers) የመሳሰሉትን (የDCPS ዲቫይሶች ወይም ቴክኖሎጂ) ያቀርባል። የDCPS አውታረ መረብ (network) እና የDCPS ቴክኖሎጂ፣ ለማቀድ፣ የትምህርት አሰጣጥ፣ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲባል ለሠራተኛ የሚሰጡ እና ለተማሪዎች ደግሞ ለትምህርታዊ ሂደቶች፣ ምርምር፣ እና የስራ እድገት ማግኛነት ሆነው ያገለግላሉ። የDCPS ተማሪ እና ሠራተኛ በቴክኖሎጂና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ የመጠቀሚያ ፖሊሲ፤ አላማው የሚከተለው ነው:

1) ለDCPS ኔትወርክ እና ለDCPS ቴክኖሎጂ፣ ተቀባይነት ያለው አጠቃቀም፣ መሠረታዊ ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ፣
2) የDCPS ኔትወርክ እና የDCPS ቴክኖሎጂን ፈቃድ የሌላቸው እና ሕጋዊ ያልሆኑ ጥቅሞች ላይ እንዳይውል ለመከላከል፣ እና
3) ከChildren’s Internet Protection Act of 2000 (CIPA)፣ ከChildren’s Online Privacy Protection Act (COPPA)፣ ከProtecting Students Digital Privacy Act፣ እና ሌሎች ከዚህ ጋር የሚሄዱ ሕጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች እና ማካሄጃዎች ጋር አብሮ የሚሄዱት ጋር ሁሉ ታዛዥ ለመሆን፤

ፖሊሲው ለሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች (በጥቅል፣ ተጠቃሚዎች) የሚውል ሆኖ፤ ‘DCPS Student Safety and Use Policy for Internet and Technology (2009)’ን የሚሸር ይሆናል።

## II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ[1]

| ምንጭ | ጥቅስ (Citation) |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ (USC) | - Children’s Internet Protection Act (CIPA), codified at 47 U.S.C. § 254(h)(5)<br>- Children’s Online Privacy Protection Act of 1998 (COPPA), codified at 15 U.S.C. § 6501 *et seq*.<br>- Neighborhood Children’s Internet Protection Act, codified at 47 U.S.C. § 254(l) |
| የፌደራል ደንቦች (CFR) | - Children’s Online Privacy Protection Rule, 16 CFR Part 312 |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ (DC Code) | - Protecting Students Digital Privacy Act of 2016, D.C. Law 21-218, codified at D.C. Code 38-831.01 *et seq*. |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች (DCMR) | - 5-B DCMR § 2500 *et seq*. – Student Discipline<br>- 6-B DCMR § 1610 – Employee Progressive Discipline |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞቻቸው

[1] Nothing in this policy shall supersede federal, state, or local law.

የ**DCPS ሠራተኛ**: ሁሉም የDCPS ተቀጣሪዎች (በሙሉ ወይም የግማሽ ሰዓት)፣ በኮንትራት፣ ድርጅቶች፣ ወኪሎች ወይም በጎ ፈቃደኞች፣ ወይም ሌላ ማንኛውም DCPSን በመወከል የሚሰራ ግለሰብ፣ የDCPS ኔትወርክ ወይም የDCPS ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚችል ማለት ነው።

የ**DCPS ኔትወርክ**: ለሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በDCPS የተሠጡ፤ የኢንተርኔት፣ የመረጃ ስብስብ (data)፣ እና የኔትወርክ ዘዴዎች

የ**DCPS ቴክኖሎጂ**: ለሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በDCPS የተሠጡ፤ ኮምፒውተሮች፣ ታብሌቶች፣ ዲቫይሶች፣ እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች

**የግል መረጃ:** ለብቻው ወይም ከሌላ ጠቃሚ የመረጃ ስብስብ (data) ጋር በአንድነት፣ መረጃዎችን በመጠቀም እንደ የግል መረጃ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። የግል መረጃ፣ የሚከተሉትን፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ሙሉ ስም፣ የቤት ወይም ሌላ የመኖሪያ አድራሻ፣ እንደኦንላይን የመገኛ መረጃነት የሚያገለግል የስክሪን (screen) ስም ወይም የመጠቀሚያ ስም (user name)፣ እና የግለሰቦችን ምስል ወይም ድምፅ የያዙ የፎተግራፍ፣ የድምፅ፣ ወይም የቪዲዮ ፋይሎች ናቸው።

**እገዳ**: ተማሪው፣ የስነ ስርዓት ቅጣትን በተከተለ ምክንያት፣ ከትምህርት ቤት መደበኛ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ እንዲወጣ ተደርጎ፣ ተማሪው በትምህርት ቤት ሠራተኛ ተቆጣጣሪዎች ጥበቃ ስር ሆኖ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲቆይ ሲደረግ፤ ወይም ተማሪው በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዳይገኝ በማድረግ በጊዜያዊነት ማገድ።

**መባረር:** ተማሪውን ከሚማርበት ትምህርት ቤት በስነ ስርዓት ችግሮች ምክንያት ከቀሪው የትምህርት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ማስወጣት።

**የስነ ስርዓት መቅጫ እርምጃዎች (Progressive Discipline)**: የሠራተኞች የስነ ስርዓት መቅጫ ዘዴ፣ በሠራተኞች የሥራ ክንውን ወይም የጠባይ ችግሮች ላይ የበላይ የአፈጻጸም ምላሽ ይሰጣል። የDCPS የስነ ስርዓት መቅጫ እምጃዎች አሰጣጥ ደረጃዎች፣ በቃል የሚደረግ ምክርን፣ ወቀሳ፣ የማረም እርምጃ፣ እና የማስጠንቀቂያ እርምጃዎችን ይጨምራል።

## IV. መስፈርቶች

### A. አጠቃላይ (General)

DCPS፣ የDCPS ኔትወርክን እና የDCPS ቴክኖሎጂን ለሠራተኞችና ተማሪዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ያቀርባል፤ ፈቃድም ይሰጣል። DCPS የቴክኖሎጂ መገኛ ምንጮችን (resources) በመስጠቱና በመፍቀዱ የተነሳ፣ በመረጃ ዘዴው ላይ ያሉ ቁሳቁሶችን ወይም በእነዚህ ዘዴዎች ላይ በሚገኙ ፋይሎች ላይ ያለውን ቁጥጥር አሳልፎ አይሰጥም። ከዚህ በታች በተገለጸው አኳሃን ካልሆነ በስተቀር፣ በDCPS ኔትወርክ ወይም በDCPS የመገናኛ ዘዴዎች ላይ በተቀመጡት ወይም በተሰራጩት መረጃዎች ላይ ከግላዊነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በማስተማመኛነት መያዝ የማይቻል መሆኑን እና፤ በDCPS ቴክኖሎጂ እና በDCPS ኔትወርክ አካውንቶቹ፣ እና በመገናኛነት በሚጠቀምባቸው በሁሉም የDCPS ኔትወርክ ላይ የተቀመጡ ፋይሎቹን፤ የማግኘት፣ የመገምገም፣ የማባዛት፣ የማስቀመጥ ወይም የማጥፋት መብት አለው። በDCPS ኮምፒውተሮች ውስጥ የተቀመጡ ወይም የDCPSን የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የተሰራጩ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶችንና ፋይሎችን፣ ልክ እንደሌላ የትምህርት ቤቱ ንብረቶች ሊታዩ ይችላሉ። የመገናኛ ዘዴውን አቋም ለመጠበቅ እና ተጠቃሚዎች በኃላፊነት እየወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የDCPS ሠራተኞች ምናልባት ፋይሎችን እና መልዕክቶችን ይገመግሙ ይሆናል። በDCPS ለተማሪዎች የተፈጠረን ወይም በDCPS ጥያቄ በተማሪዎች የተፈጠረን፣ ሁሉንም የተማሪዎች አካውንት የDCPS ሠራተኞች ቁጥጥር ሊያደርጉበት ይችሉ ይሆናል።

### B. ኔትወርክ፣ ኢሜል እና አፕሊኬሽኖች

1. ኔትወርክ/አውታረ መረብ (Network)

የDCPS አውታረ መረብ (network) እና የDCPS ቴክኖሎጂ፣ ለማቀድ፣ የትምህርት አሰጣጥ፣ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲባል ለሠራተኛ የሚሰጡ እና ለተማሪዎች ደግሞ ለትምህርታዊ ሂደቶች፣ ምርምር፣ እና የስራ እድገት ማግኛነት ሆነው ያገለግላሉ። በDCPS ኔትወርክ አማካኝነት ለሠራተኞች እና ተማሪዎች ውስጣዊ የማግኘት መብትን በመስጠት፣ ወደ የDCPS መረጃዎችና የመረጃ ምንጮች፣ በDCPS የተፈቀዱ ማመልከቻዎችን፣ እና ውጫዊ የማግኘት መብቶችን በኢንተርኔት ያስገኛል።

የDCPS ኔትወርክን ማግኘት፣ ተማሪውን በብቸኝነት በትምህርት፣ በምርምር፣ እና በሥራ እድገት ለመደገፍ የኢንተርኔት አገልግሎት ለተማሪዎች በመስጠት ይረዳል። የDCPS ኔትወርክን መጠቀም ልዩ እድል እንጂ መብት አይደለም። ማንኛውም የዚህ ፖሊሲ ክፍል ወይም ተዛማጅ የሆኑ ፖሊሲዎችን የሚጥሱ ሠራተኞችና ተማሪዎች፣ ይህንን የDCPS ኔትወርክ የመጠቀም ልዩ እድል እንዲሰረዝባቸው ሊያደርጋቸውና የስነ ስርዓት መቅጫ እርምጃንም ሊያስከትል ይችላል።

የኔትወርክ ማግኘት እና ባንድዊድዝ (bandwidth) ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው፣ ለስርዓተ ትምህርትና ማከናወኛ አገልግሎቶች ነው። DCPS የኔትውርክ ባንድዊድዝን ቅድሚያ የመስጠትና የተወሰኑ በስርዓተ ትምህርቱና ክንውኖቹ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ የኔትወርክ እንቅስቃሴዎችን የመገደብ መብቱ የተጠበቀ ነው። የኔትወርኩ ተጠቃሚዎች፣ አግባብነት የሌላቸው ወይም ሕገወጥ ይዘት ያላቸውን ነገሮችን፣ የሚከተሉትን፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ፣ እንደ የወሲብ ክንውን (pornographic)፣ ፀያፍ፣ ሕገወጥ፣ ወይም ዓመጽን አነሳሽ የሆኑ ነገሮችን በDCPS ኔትወርክ እንዳይጠቀሙ ይከለከላል።

DCPS በኔትወርክ አገልግሎቱ ላይ የሚሰጠው ተግባራት ወይም ጥራት ሁሉ ከማንኛውም ስህተት ወይም ብልሽት ነፃ መሆኑን ሙሉ ለሙሉ ዋስትና አይሰጥም። ለማንኛውም አቤቱታዎች፣ የጠፉ ነገሮች፣ ጉዳቶች፣ ክፍያዎች፣ ወይም ኔትወርኩን ወይም አካውንቶቹን በመጠቀም የሚመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ላይ፣ DCPS ኃላፊነት አይወስድም። በማንኛውም የኔትወርክ አጠቃቀም የሚመጣ የክፍያ መጠየቂያ፣ የግለሰቡ የግል ሸክም ይሆናል። ከDCPS ድህረ-ገጽ ወይም ከኮሎምብያ ዲስትሪክት መንግስት ድህረ-ገጽ ለተገኘ መረጃ ካልሆነ በስተቀር፤ የመረጃ ዘዴውን በመጠቀም የሚገኙ መረጃዎች፣ ትክክለኛነት ወይም ጥራት ላይ፣ DCPS ኃላፊነት አይወስድም። ማንኛውም በኔትወርኩ ወይም ከኢንተርኔት የሚገኙ መልዕክቶች፣ የፀሐፊውን የግል አመለካከትን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን መረዳት እና የDCPS፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክት መንግስት፣ የተባባሪዎቻቸው፣ ወይም ተቀጣሪዎች እንዳልሆኑ ይገንዘቡ።

2. ማጣራቶች እና ክትትል

የልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ድንጋጌ (Children’s Internet Protection Act (CIPA)፤ በሚጠይቀው መሠረት፣ DCPS ተማሪዎችን መጠበቅ እና ስለኦንላይን ስጋቶች፣ አግባብነት የሌላቸው ይዘቶችን መዝጋት፣ እና በትምህርት ቤት ኔትውርኮች[2] ላይ ለአቅመ አዳም ያልደረሱን አጠቃቀማቸው ላይ ክትትል በማድረግ ያተምራል።

ለአቅመ አዳም ላልደረሱ ፀያፍ፣ የወሲብ ክንውን (pornographic)፣ ወይም ጉዳይ የሚያስከትሉ የምስል ማሳያዎችን ከኢንተርነት መገኛዎች ለማገድ ወይም ለማጣራት፣ DCPS የቴክኖሎጂ መከላከያዎችን ይጠቀማል። ከዚህ በታች በክፍል IV.G ከተገለጸው በስተቀር፣ DCPS የተማሪዎችን የኦንላይን እንቅስቃሴዎች እና የሚያዩዋቸውን ነገሮች በመቆጣጠርና በመከታተል፣ እና ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን ወይም ፋይሎችን፤ በማግኘት፣ መገምገም፣ ማባዛት እና ማስቀመጥ ወይም ማጥፋት፤ እንዲሁም አስፈላጊነቱ ከታመነ፣ ለሌሎችም የማሳወቅ መብቱ የተጠበቀ ነው። የተማሪዎችን የዲጂታል ግላዊነት ድንጋጌን መጠበቅ (Protecting Students Digital Privacy Act (ከታች ክፍል IV.G ይመልከቱ)፤ በተቋቋመው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣ የDCPS ንብረትን፣ የDCPS የኮምፒውተር ኔትወርክን ወይም ኢንተርኔትን፣ ፋይሎችን፣ ወይም ኢሜልን በዚሁ ኔትወርክ ውስጥ ሆነው ሲጠቀሙ፤ ተማሪዎች ምንም ዓይነት የግላዊነት ስሜት ሊኖራቸው አይችልም።

እንዲሁም DCPS የደህንነት የአመራር ዘዴን ተጠቅሞ፣ በኦንላይን የተማሪ የፋይል ማከማቻ፣ ገቢና ወጪ የDCPS ኢሜልን፣ የDCPS ኢሜል አባሪዎችን (attachments)፣ እና ወደ ድህረ-ገጽ ማገናኛ ሊንኮችን ይዘታቸውን ጥናት እና ምርመራ ያደርጋል። ይህ ዘዴ ጎጂነት አላቸው ተብሎ የሚታሰቡ ይዘቶችን እና ምስሎችን ያግድና በአስቸኳይ ሁኔታዎች ጥቆማ ስር፣ ለራስ ወይም ለሌሎች እንደ ስጋቶች እና ጥቃቶች ማስጠንቀቂያ ለDCPS ሠራተኛ ያሳውቀዋል።

3. አፕሊኬሽኖች (Applications)

የልጆች በኦንላይን ግላዊነት ጥበቃ ድንጋጌ (The Children’s Online Privacy Protection Act (COPPA)፣ የድህረ-ገጹ ተቆጣጣሪዎች ወይም ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች የኦንላይን አገልግሎቶች የተመሩ፣ እና ከ13 ዓመት በታች ከሆኑ ልጆች የግል መረጃዎችን በኦንላይን የሚሰበስቡ ትክክለኛ እውቀት ያላቸው የሌሎች ድህረ-ገጾች ተቆጣጣሪዎች፣ መረጃውን ከመሰብሰባቸው፣ ከመጠቀማቸው ወይም የልጆቹን[3] የግል መረጃዎች አሳልፈው ከመስጠታቸው በፊት፣ የወላጅ ፈቃድ የተሰጠበትን ስምምነት ማግኘት ያስፈልጋቸዋል።

---

[2] 47 U.S.C. 254(h)(5)(B).

[3] *See* 16 CFR Part 312.5. This requirement also applies to any material change in the collections, use, or disclosure practices to which a parent has previously consented. Operators must also give parents the option to consent to the collection and use of the child's personal information without consenting to disclosure of his or her personal information to third parties.

ለDCPS መገልገያና ጥቅም እንዲውል እና ለሌላ ምንም ዓይነት የንግድ ስራ ላይ የማይውል፣ የግል መረጃዎችን ከድህረ-ገጽ ወይም ከኦንላይን ለመሰብሰብ ኮንትራክት ሲገባ፣ ከDCPS የማግኛ የፈቃድ ስምምነት ማግኘት የሚችልና በቀጥታ የወላጆችን[4] የፈቃድ ስምምነት ማግኘት አያስፈልገውም። ሁሉም የCOPPA-ተገዢ የሆኑ ድህረ-ገጾች እና የኦንላይን አገልግሎቶች፣ DCPS ኮንትራት የወሰደባቸው እና/ወይም ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ተማሪዎች ማግኘት እንዲችሏቸው የተደረጉ፣ የእያንዳንዱ አቀናባሪ የሆነን የግል ፖሊሲ ሊንክን ጨምሮ፣ እና ወላጆች ካልፈለጉ ለመውጣት (opt out) ምን ዓይነት ሂደትን መከተል እንደሚገባቸው የሚያሳይ፣ የDCPS የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ዝርዝር (inventory) በሆነው የDCPS ድህረ-ገጽ ላይ የቀረበውን፣ የስምምነት ማስታወቂያ ለወላጆች ያቀርባል። ለnon-COPPA ተገዢ ያልሆኑ ድህረ-ገጾችን እና አገልግሎቶችን፣ ወይም ማንኛውም በCOPPA-ተገዢ ድህረ-ገጾችን እና አገልግሎቶችን ለመጠቀም፣ ቤተሰቦች የግል መረጃ እንዲሰበሰብ ባልፈቀዱበት ሁኔታ፣ ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ተማሪዎችን የDCPS ሠራተኞች ለተማሪዎች መፍቀድ አይችሉም።

4. የማግኘት ፈቃድን መቆጣጠር (Access Control)

DCPS የደህንነት ጥበቃ ያለው የማግኘት ፈቃድ ቁጥጥር እርምጃዎችን የሚወስደው፣ ሁሉም ተገቢ የሆነው ኔትወርክ እና ቴክኖሎጂን የማግኘት ፈቃድ፣ ለሁሉም DCPS ተጠቃሚዎች በተገቢ ሁኔታ መሰጠቱን እና ፈቃድ የሌላቸው እና ስጋት ፈጣሪ ናቸው ተብለው የሚገመቱትን ቆልፎ ለማስወጣት (lock out) ነው። DCPS የተማሪዎችን የማግኘት ፈቃድ፣ እንደ DCPS ኔትወርክ፣ የDCPS ኢሜል አካውንቶች፣ እና የDCPS ፍቃድ ያላቸው አፕሊኬሽኖችን እንደየክፍል ደረጃ እና ትምህርት ቤት ወይም አስተማሪ ጥያቄ መሠረት እንደሚከተለው ይመድብላቸዋል:

- *ኔትወርክ/አውታረ መረብ (Network):* ሁሉም ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ የየግል ማስረጃዎች እና የሚስጥር መግቢያ ኮዶችን (passwords) ይሰጣቸዋል። ሁሉም ተማሪዎች የራሳቸው ሆኖ ለግል መጠቀሚያ የተሰጣቸውን ማስረጃዎች እና የመግቢያ የሚስጥር ኮዶችን (passwords) በመጠቀም መግባት (log in ማድረግ) **<u>አለባቸው።</u>**
- *ኢሜል:* በ9ኛ ክፍል እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች፣ የዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course)ን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ፣ የDCPS ኢሜል አካውንት ይሰጣቸዋል። በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ እንደ DCPS ሠራተኛው አስተያየት መሠረት፣ የዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course)ን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ፣ የDCPS ኢሜል አካውንት ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል። የተወሰነ ዓይነት ጉደተኝነት ያላቸው ተማሪዎች፤ ፈተና የማግኘት እና የክፍል ውስጥ ማመቻቻዎችን በየግል የትምህርት ዕቅዳቸው (Individualized Education Plan (IEP) ውስጥ እንደተዘረዘረው፤ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ (Read aloud)ን እና የተደጋገመ ትዕዛዛትን፣ በተቀነሰ-ሁኔታ መነበብ የሚችሉ ጽሁፎች እና የይዘትን ቀላል ማድረግን እና ሌሎች ማመቻቻዎችን አካትቶ ሊይዝ የሚችለውን በመጠቀም፤ የዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course)ን ሊያጠናቅቁ ይችላሉ።
- አፕሊኬሽኖች (*Applications*): DCPS በተወሰነ ደረጃ ፈቃድ ያገኙ አፕሊኬሽኖችን ለሁሉም የDCPS ሠራተኞች እና ተማሪዎች እንዲጠቀሙ መንገድ ይሰጣል። የሠራተኞች የማግኘት ፈቃድ የሚሰጠው እንደ ስራ ኃላፊነታቸው እና ለአንዳንድ አፕሊኬሽኖች በርዕሰ መምህሩ ጥያቄ መሠረት ነው። ለተማሪዎች የማግኘት ፈቃድ የሚሰጣቸው አፕሊኬሽኖች፣ ፈቃድ የተሰጣቸውን መጠቀሚያዎች ነው። በትምህርት ቤቱ እና በአስተማሪው ጥያቄ መሠረት፣ ተማሪዎች ፈቃድ ከተሰጣቸው መጠቀሚያዎች ውጪ ሌሎች አፕሊኬሽኖችን ማግኘት ይችሉ ይሆናል።

5. የሚስጥር ቁልፎች (Passwords)

የDCPS ተጠቃሚዎች በሙሉ፣ ወደ ትምህርት ቤቱ ኮምፒውተሮች፣ ኔትወርኮች፣ እና የኦንላይን መገልገያ ዘዴ ሲገቡ (logging)፣ በDCPS የሚስጥር ቁልፍ (password) መስፈርቶች ከለላ ስር ሆነው መጠቀም ያስፈልጋቸዋል። ተጠቃሚዎች የሚስጥር ቁልፋቸውን (password) ከሌላ ጋር ማጋራት ፈቃድ የሌላቸው እና የሚስጥር ቁልፎችን (password) ወይም ሌላ የግል መረጃዎችን የሚጠይቁ፣ የኢሜል ማታለያዮች (email scams) ለማስወገድ የተቻለውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። በተወሰነው የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች፣ በዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course) ውስጥ እንዲካፈሉና፣ እነዚህን ማጭበርበሮችን (scams) እንዴት ማስወገድ እንደሚችሉ እና ሌሎች ጥሩ የሆኑ የሳይበር ልምዶችን (cyber practices)ን ይማራሉ።

የሚስጥር መግቢያ ኮዳቸውን በመጠቀም፣ ተማሪዎች በራሳቸው ማስገባት ካልቻሉ ወይም ማስታወስ ካልቻሉ፤ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኘውን ተማሪን የሚረዳው አዋቂ ሰው እርዳታ ያደርግላቸዋል።

---

[4] More information about complying with COPPA is available from the Federal Trade Commission here: https://www.ftc.gov/tips-advice/business-center/guidance/complying-coppa-frequently-asked-questions.

የተከለከሉ ነገሮችን የመጠቀም ቅጣቶች፤ የኔትወርክ ማግኘት ግደባዎችን ወይም የአካውንቶች መሰረዝን ሊያስከትሉ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ጥሰቶቹ ምናልባት ለተማሪዎቹ፣ በስነ ስርዓት እና/ወይም የሕግ እርምጃዎችን የሚያስከትሉ ሆነው፣ ለተወሰነ ጊዜ መታገድ፣ ማስወገድ፣ እና በወንጀለኛነት መከሰስን ይጨምራል።

6. የኦንላይን ደህንነት ጥበቃ፣ ዲጂታል ዜግነት፣ እና ሳይበርሴኩሪቲ (Cybersecurity)

DCPS ለተማሪዎች ዓመታዊ የዲጂታል ዜግነት እና የኦንላይን ደህንነት ጥበቃ ትምህርቶችን ይሰጣል። የዲሲ መንግስት (DC Government)፣ የዲሲ ዋናው የቴክኖሎጂ ቢሮ ባለስልጣን (DC Office of the Chief Technology Officer) እና/ወይም DCPS፤ ከሳይበርሴኩሪቲ ወይም ተያያዥ የሆኑ ርዕሶች ጋር የሚሰጡ የተቀጣሪ ስልጠናዎችን፣ ሠራተኞች እንዲወስዱ ይጠይቅ ይሆናል። ስልጠናዎቹን ጊዜውን ጠብቆ ለማጠናቀቅ አለመቻል፣ የስነ ስርዓት መቅጫ እርምጃዎች (progressive discipline) ሊያስከትል ይችላል።

7. ቴሌሄልዝ (Telehealth)/ቴሌሜዲሲን (Telemedicine) ማግኘት

የDCPS ሠራተኞች እና ተማሪዎች፣ የቴሌሄልዝ (telehealth) ክፍለጊዜዎችን በDCPS ዲቫይሶች ላይ ለማግኘት ይፈቀድላቸዋል። ምንም እንኳን ዲስትሪክቱ በቀጣይነት የቴሌሄልዝ (telehealth) ክፍለጊዜዎችን የመቆጣጠር ፍላጎት ባይኖረውም፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች የመረጃ ስብስቡን (data)፣ በትምህርት-ቤት የተሰጡ ዲቫይሶች ላይ፣ ይህም በዲቫይሱ ሃርድ-ዲስኮች ላይ እንዲቀመጡ የተደረጉ ሌሎች የሕክምና መረጃዎችን ጨምሮ፤ እንዲፈትሹ እና የተማሪ እንቅስቃሴን እንዲቆጣጠሩ፤ የፌደራል ሕግ ይጠይቃል። **<u>የቀጥታ-ስርጪት የቴሌሄልዝ (telehealth) ክፍለጊዜ፣ ቁጥጥር አይደረግበትም።</u>** ሚስጢራዊነት ያላቸው የመረጃ-ስብስብ (data)፣ በዲቫይሶች ሃርድ-ድራቮች ላይ ተቀምጦ ከሆነ፣ ዲቫይሶቹ ወደ ዕቃ-ስብስብ (inventory) ሲመለሱ መረጃዎቹ ይጸዳሉ።

8. ቪዲዮ ኮንፈራንስ ማድረግ

የቪዲዮ-ኮንፈረንስ የሚካሄደው፣ የDCPS ሠራተኛ እና ተማሪዎች በተለያየ ቦታዎች ሆነው እርስ-በእርስ ግንኙነትን በዚያኑ ጊዜ በሚሰራጭ ድምጽ እና እይታ (real-time sound and vision) የቪዲዮ-ኮንፈራንስ አፕሊኬሽን በመጠቀም ሲያካሂዱ ነው። አስተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ የቪዲዮ-ኮንፈረንሱን መቅዳት እና ለራሳቸው እና ለተማሪዎች በኋላ እንዲገኝ ለማድረግ ይችላሉ።

ሠራተኞች ስለ ግል-መረጃዎችን የሚገልጹ መረጃን ስለተማሪው በቪዲዮ-ኮንፈራንሱ ክፍለ-ጊዜዎች ጊዜ መግለጽ የለባቸውም።

አስተማሪዎች እና ተማሪዎች፣ ማንኛውንም ተገቢ-ያልሆነ ወይም አሳሳቢ የሆኑ ባህሪያት፣ በቪዲዮ-ኮንፈረንሱ ጊዜ፣ የDCPS ቢሮን ታማኝነት በሚነካ ሁኔታ ሲፈጠሩ፣ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ የDCPS የተቀጣሪ ሠራተኞች መብቶች እና ኃላፊነቶች ፖሊሲን፣ የDCPS የማህበራዊ ሚድያ ፖሊሲን፣ እና በሠራተኛ-ተማሪ ግንኙነቶችን በተመለከተ ሌላ ማንኛውም ተገቢ- የሆኑ ፖሊሲዎችን መከተል አለባቸው።

## C. ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተሮችን፣ ላፕቶፖችን፣ ታብሌቶችን ጨምሮ)

1. የዲቫይስ እርዳታ (Device Support)

DCPS መሠረታዊ የሆኑ፣ የመጫን (installation)፣ የማቀናበር (synchronization)፣ እና የሶፍትዌር እርዳታን ከDCPS-ለተሰጡ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ይሰጣል። እነዚህ ዲቫይሶች፣ የሶፍትዌር አዲስ እና ማሻሻያዎችን ለመጫን እና/ወይም ለዕቃ ክምችት ቆጠራ (inventory) ሲባል፣ በመደበኛ ሁኔታ ከDCPS ኔትወርክ ጋር መገናኘት አለባቸው። ሁሉም ከDCPS-ለተሰጡ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች፣ በሚጠፉ ወይም በሚሰረቁ ጊዜ ያልተፈቀደ አጠቃቀምን ለመከላከል እንዲያስችል በሚስጥር ቁልፍ (Password) የተጠበቁ መሆን አለባቸው።

2. ጉዳት ሲደርስ፣ መጥፋት እና መሰረቅ

ሠራተኞች፣ ለDCPS ቴክኖሎጂ ታማኝ አገልጋዮች የሆኑ እና በቸልተኝነት በንብረቶች ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች፣ ጥፋት ወይም ስርቆት ምክንያት የገንዘብ ኃላፊነት አለባቸው። የቸልተኝነት ምሳሌዎች የሚጨምሩት፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ እንደ:

- የDCPS ቴክኖሎጂ የሆነውን በተሽከርካሪ ወይም ሌላ ቦታ በመተው በሙቀት፣ በብርድ ወይም በእርጥበት ምክንያት ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ፣
- መጠጦችን ወይም ምግብ በማፍሰስ ጉዳት ማድረስ፤ ወይም
- የDCPS ቴክኖሎጂን ብቻውን በማስቀመጥ ወይም ጥበቃ በሌለው ቦታ በመተው እንዲሰረቅ ማድረግ።

ዲቫይሱን ከጉዳት፣ ከመጥፋት ወይም ከመሰረቅ ለመከላከል፣ ተማሪዎች ተገቢ የሆነውን እርምጃ ሁሉ መውሰድ አለባቸው። ተማሪዎች ላደረሱት ጉዳት የሚደረገው የስነ ስርዓት ምላሾች፣ የDCPS የስነ ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎችን በተከተለ ሁኔታ ይወሰናል። ይህ የክትትል-ምርመራ፤ ተማሪው ስለ ዲቫይስ እንክብካቤ፣ ዕድሜ እና ማንኛውንም ጉዳተኝነትን ጨምሮ፤ መረዳት መቻሉና አለመቻሉ ላይ የሚያደርሰውን ተጽዕኖ ላይ ባሉትን ምክንያቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል። ከግዴለሽነት ወይም ሆን-ተብሎ ከተደረገ የጥፋት ጉዳት ማድረስን ጨምሮ፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ የቀረቡ ምሳሌዎች:

- በዲቫይሱ ላይ በማይጠፋ ማርከር (permanent marker) በመጠቀም መሳል፣ ቃላቶችን/ምስሎችን ስለታማ በሆኑ ነገሮች በመፋቅ መፃፍ ወይም መሳል፣ ወይም በዲቫይሱ ላይ በእንሰሳት የተነከሰበት ምልክቶች (animal bite marks)፤
- በተለያዩ ቦታዎቹ ላይ በሚከተሉት ምክንያት ጉዳት ሲደርስበት፤ ዲቫይሶቹ በሚገባ ስላልተያዙ ወይም እንክብካቤ በማጣቸው ምክንያት (ለምሳሌ፤ ስክሪኑ መሰንጠቅ፣ ኪቦርዱ (keyboard) መበላሸት፣ ቁልፎቹ (keys) ተነቅሎ ሲጠፋ፣ እና የላፕቶፑ ሽፋን የተመታ መሆኑን በተለያዩ ቦታዎቹ ላይ ሲታይ ወይም ላፕቶፕ/ታብሌት ተገነጣጥሎ በተለያየ-ቁርጥራጭነት ሲመለሱ፤
- ሃይለኛ የሆነ ጉዳት፣ ስለታም ነገር በመጠቀም ወይም ከባድ እቃ(ዎችን) በመጠቀም የተነሳ ጉዳት ሲደርስ፣ ወይም በእቃ(ዎቹ) በላፕቶፑ USB ላይ ወይም የኤሌክትሪክ መሰኪያው ላይ ተጭኖት ጉዳት ሲደርስበት፤
- ዲቫይሱ በውሃ ውስጥ ወይም በፈሳሽ-ነገሮች ውስጥ ተነክሮ ነበር።

ከግዴለሽነት ወይም ሆን-ተብሎ ከተደረገ የጥፋት ጉዳት ማድረስ ምክንያት በዲቫይሶቹ ላይ ጉዳት ሲደርስ፣ የስነ-ስርዓት መቅጫ ምላሾቹ፣ በDCPS የስነ-ምግባት ህጎች እና ፖሊሲዎች ስር እና በዚህ ተገቢ-የሆነ የመጠቀሚያ ፖሊሲ (Acceptable Use Policy)፣ የሚወሰን ይሆናል። ከተለመደ የማርጀት የተነሳ (wear and tear) ወይም ሆን-ተብሎ ያልሆነ አደጋዎች ከሚደርሱ ጉዳቶች፣ ተማሪዎች ላይቀጡ ይችሉ ይሆናል። ከተለመደ የማርጀት የተነሳ (wear and tear) የጥፋት መድረስ ምክንያት የተፈጠሩ እነዚህ ምሳሌዎችን ጨምሮ፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰን:

- ከኪቦርዱ (keyboard) ላይ አንድ ቁልፍ (key) ወይም ቁልፎች ሲጠፉ፤
- ዲቫይሱ በመውደቁ ምክንያት፣ ስክሪኑ ከተሰነጠቀ፤
- ዲቫይሱ በወደቁ ምክንያት የተፈጠረ ሊሆን የሚችል፣ እንደ በስክሪኑ የጎን ማዕዘ/ጎኖች ላይ በሆነው የዲባይሱ አነስተኛ ክፍል ተለይቶ የሚታይ ጉዳት፤
- በኪቦርዱ (keyboard) ላይ፣ በድንገት ፈሳሽ ነገር ሲፈስበት፣ ወይም
- በኃይል-መጨመር ምክንያት የሚከሰት ብልሽት።

የDCPS ቴክኖሎጂ በሚጠፋ፣ በሚሰረቅ፣ ወይም ጉዳት በሚደርስበት ወቅት፣ ተጠቃሚዎች ወዲያውኑ ለDCPS ሠራተኛ ማሳወቅ አለባቸው። DCPS የጠፋውን ንብረት ለማግኘት እና ዲቫይሱ የያዘውን ማንኛውንም መረጃ በደህንነት እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳል። DCPS፣ የቦታ መጠቆሚያ ሶፍትዌርን (location tracking software) በዲቫይሱ ላይ ማስማራትን በመምረጥ፤ እንደጠፋ ወይም እንደተሰረቀ የተጠቆመውን ዲቫይስ ለማግኘት ይጠቀምበታል።

3. ለአንድ ሌሊት (Overnight) ወይም በቤት ውስጥ (At-Home) በተማሪዎች መጠቀም

የDCPS ትምህርት ቤት ሠራተኞች ለአንድ ሌሊት (overnight) ወይም በቤት ውስጥ (at-home) መጠቀሚያ የሚሆን የDCPS ዲቫይሶችን፣ ከቻንስለሩ ወይም ከቻንስለሩ ተወካይ በፅሁፍ የሚያረጋግጥ ፈቃድ ሳያገኙ ለተማሪዎች መስጠት አይችሉም። የDCPS ተማሪዎች እና ወላጅ/አሳዳጊ፤ ከዚህ ጋር አባሪ የሆነው የተማሪ ቴክኖሎሚ በኃላፊነት መጠቀሚያ ስምምነትን፣ በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ለአንድ ሌሊት-አሳድረው (overnight) ለመጠቀም ዲቫይስ ከመመደቡ በፊት፤ መፈረም አለባቸው። ይህን ዓይነት የፕሮግራም ፈቃድ በሚከሰት ጊዜ፣ ፕሮግራሙን የሚከታተለው የDCPS ሠራተኛ ግላዊነትን የጠበቀ መስፈርቶች ስር፣ በተማሪዎች የዲጂታል ግላዊነት ጥበቃ ድንጋጌ (Protection of Student Digital Privacy Act. [5]) ስር ሕጉን መከተሉን ማረጋገጥ አለበት።

[5] Specifically, DC Code § 38-831.03(a).

እንደ ኢጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology) ሆኖ የተመደበው ቴክኖሎጂ፣ የIEP ቡድኑ፤ ቻንስለር ወይም ተወካያቸው ያልሆነ፣ ተማሪው እነዚህ እገዛዎች ትምህርታዊ ስራዎቹን በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ (ለምሳሌ የቤት ስራ፣ ግንኙነቶችን ለማድረግ) እንደሚያስፈልጉት ከወሰኑ፤ ከተማሪው ጋር ወደ ቤት ሊወስዱ ይችላሉ።

### D. ባሕሪያት (Conduct) እና ተቀባይነት ያለው መጠቀሚያ

የDCPS ኔትወርክ እና የDCPS ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች ሁሉንም የዲሲ መንግስት (DC Government)፣ የዲሲ ዋናው የቴክኖሎጂ ቢሮ ባለስልጣን (DC Office of the Chief Technology Officer) እና DCPS ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን፣ እና መመሪያዎችን ለመከተል ተስማምተዋል። ሠራተኞች አላግባብ አጠቃቀም ወይም የፕሮቶኮሎች መጣሶችን፤ ለአስተማሪዎች፣ አግባብ ላላቸው ኃላፊዎች፣ አስተዳደሮች፣ ወይም ለማዕከላዊ ቢሮ ሠራተኞች ወዲያውኑ አላግባብ አጠቃቀሙን ወይም ጥሰቱን[6] እንዳወቁ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ተጠቃሚዎች፣ የDCPS ኔትወርክ ወይም የDCPS ቴክኖሎጂን፣ ኢንተርኔት ማግኘት፣ ኢንትራኔት(intranet)፣ የትብብር መሣሪያዎች (collaboration tools)፣ የጅምላ (bulk) መገናኛ መሳሪያ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ኢሜል ለመጠቀም፣ ለመቅዳት፣ ለማጋራት፣ አፕሎድ ለማድረግ (upload)፣ ለመለጠፍ፣ ሜል (mail)፣ ማሳያ፣ ማስቀመጥ ወይም ሌላ ማስተላለፊያ መንገድን፣ በማንኛውም ይዘት፣ መገናኛ ወይም መረጃ፣ ከሌሎች ተቀባይነት ከሌላቸው መጠቀሞች ጋር በተያያዘ መጠቀም አይችሉም:

1. ጥላቻ ያለበት፣ መነዝነዝ፣ ማስፈራራት፣ አጥፊነት ወይም ስም ማጥፋት ነው፣
2. አጸያፊ ወይም በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሄራዊ አመጣጥ፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በግል አቋማዊ ገጽታ፣ ፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በመማሪያ ቦታዎች፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ የዘር አመጣጥ መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ በቤተሰብ ውስጥ ባለ ወንጀል ሳቢያ ሰለባ የመሆን ሁኔታ፣ በመኖሪያ ወይም በንግድ ቦታ ሳቢያ፣ የሰለባ ወይም የሰለባው የቤተሰብ አባል መሆን – በቤት ውስጥ ሁከት፣ በወሲባዊ ጥቃት፣ ወይም በማሳደድ፤ እነዚህን ሁሉ መሠረት በማድረግ በሰው ላይ አድልዎ ማድረግ፤
3. ማንኛውንም የወንጀል ጥፋትን ማሴር ወይም ማስፋፋት፣ ወይም ለሲቪል ተጠያቂነት ማነሳሳት፣ በማንኛውም በስራ ላይ በዋለ ሕግ ስር፣ የU.S. የላኪ ቁጥጥር (export control) ሕጎች ወይም የU.S. ፓተንት (patent)፣ የንግድ ስያሜ (trademark) ወይም የቅጂ ሙብቶች (copyright) ሕጎችን ጨምሮ ካለምንም ግደብ፤
4. ማንኛውም ጸያፍ ወይም ለወሲብ ክንውን (pornographic) አገልግሎት የሚውል፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ማስተላለፍ፣ ማውጣት ወይም ወራዳ፣ ጸያፍ፣ ወይም የወሲባዊ ግልፅ ይዘት ያላቸውን ነገሮች የማሳየት ጥቅም ላይ ለማዋር መስራት ወይም መደገፍ፤
5. ሁከትን ለማነሳሳት በማሰብ፣ የግል ጥቃት ወይም አካላዊ ጉዳት ለማድረስ፣ ወይም ወይም ለመነዝነዝ፣ ለማስፈራራት ወይም ሌላ ግለሰብን ለማገድ በማሰብ መረጃዎችን በማዘጋጀት ለማነሳሳት ወይም ለማሰራጨት መሞከር፣
6. ቫይረስ፣ ትሮጃን ሆርስ (trojan horse)፣ ራንሳምዌር (ransomware) ወይም ሌላ ጉዳት የሚያስከትሉ ይዘቶች ያላቸው ወይም ተንኮል አዘል ኮድን መያዝ፣
7. ጀንክ ሜል (junk mail)፣ ፊሺንግ (phishing) ስፓም (spam) ወይም ፍቃድ የሌላቸውን ኢሜሎች ለማሰራጨት ማነሳሳት፣
8. የማንኛውም የሌላ ኮምፒውተር ወይም ኔትወርክ የደህንነት ጥበቃን መጣስ ወይም ያልተፈቀደ የማግኘት ዘዴን ወይም ማንኛውንም የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን የማክሸፍ ዘዴ ሙከራ በማድረግ ማነሳሳት፣
9. የሌላ የDCPS ኔትወርክ ተጠቃሚን አካውንት፣ ፋይሎች ወይም የመረጃ ስብስብ (data) ውስጥ መግባት፣ ወይም ፋይሎቻቸውን፣ የመረጃ ስብስቡን (data) ወይም የሚስጥር ቁልፎችን (passwords) መቀያየር፣
10. ማንኛውንም በሕይወት ያለ ወይም የሞተን ሰው፣ ድርጅትን፣ ንግድን፣ ወይም ሌላ አካልን አስመስሎ መገኘት፤
11. በDCPS ኔትወርክ ወይም ቴክኖሎጂ ላይ፤ ክንውኖቹን ማጣጣል፣ የደህንነት ጥበቃው ላይ አደጋን መፍጠር ወይም ካልሆነ ደግሞ ታማኝነትን ወይም ቀልጣፋ ክንውንኖቹን ማስፈራራት፣
12. የDCPS ኔትወርክን ወይም ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ፍቃድ ያለው ተጠቃሚ መከልከል፣
13. የDCPS ቴክኖሎጂን ወይም የDC ኔትወርክን ፍቃድ ካላቸው በላይ በሆነ ሁኔታ ማግኘት፣
14. ወደ DCPS የኔትወርክ ዘዴ፣ ባልተፈቀደ ሁኔታ ወይም ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ ገብቶ መጠቀም፣
15. ሚስጢራዊ ወይም ድርጅታዊ የሆኑ መረጃዎችን፣ የተማሪ የመዝገብ መረጃን ጨምሮ፣ ካለፈቃድ ወይም ትክክለኛ የጥበቃ እርምጃዎች ሳይወሰዱ አሳልፎ መስጠት፣

[6] More information about filing reports and complaints is available Section V.

16. በግላዊነት ሊለዩ የሚችሉ የተማሪ መረጃዎችን፣ ቪዲዮዎችን እና ፎተግራፎችን ካለፍቃድ ወይም ትክክለኛ የጥበቃ እርምጃዎች ሳይወሰዱ አሳልፎ መስጠት ወይም ማስተላለፍ፣
17. ስለተማሪዎች ወይም የDCPS ሠራተኛን ሚስጢራዊ የሆኑ መረጃዎች፣ የዲሲ ሕግን፣ የፌደራል ሕግን፣ ደንቦችን፣ ፖሊሲ ወይም መመሪያ በመጣስ ማጋራት፣
18. የDCPS ኢሜል አድራሻዎችን ወይም ማሰራጫ ዝርዝሮችን ይህንን ፖሊሲ ወይም ሌላ የDCPS ፖሊሲዎችን በሚጥስ ሁኔታ ማጋራት፤
19. ማንኛውም ዓይነት ውርርድን ወይም ቁማርን ማድረግ ወይም ማነሳሳት፣
20. ፍቃድ የሌላቸው ጨዋታዎች (games)፣ ፕሮግራሞች፣ ፋይሎች፣ የኤሌክትሪክ ሚዲያ፣ እና/ወይም ለብቻው የቆመ አፕሊኬሽኖች (stand-alone applications)ን፣ በDCPS ኔትወርክ ላይ አደጋ ሊፈጥር የሚችሉ ነገሮች ከኢንተርኔት ማውጣት፣ ማሰራጨት፣ ዳውንሎድ ማድረግ እና መጠቀም፤
21. ፍቃድ በሌለው በማንኛውም ዓይነት የዕጣ-ቲኬት ማውጣት (raffles) ወይም የገንዘብ ማሰባሰቢያዎችን (fundraisers) ማስተዋወቅ ወይም መካፈል፣
22. በህብረት የሚሰሩ ፖሊቲካዊ (partisan political) እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በማንኛውም ሁኔታ ማስተዋወቅ ወይም መካፈል፣
23. በውስጥ ፖለቲካ ወይም የምርጫ እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት ያለው ማኅበር ወይም ሌላ ድርጅቶችን የሚወክል ተቀጣሪን በማንኛውም መንገድ ማስተዋወቅ ወይም ከእነርሱ ጋር አብሮ-መካፈል፣
24. በግል ንግድ፣ የሺያጭ ወይም ሌላ እንቅስቃሴዎችን፣ በግል ገንዘብ ማግኛነት መሰማራት፣
25. የሌላን-ተጠቃሚ የሚስጥር ቁልፎችን (passwords) ወይም የደህንነት ጥበቃ ዘዴ መረጃን በተመለከተ፣ ባልተፈቀደ-ሁኔታ ማሰራጨት፣
26. በDCPS ኔትወርክ ወይም ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ዘዴዎች ላይ የሚገኝ የመረጃ ስብስብ (data) ላይ፣ በውሸት፣ በመነካካት ወይም ፈቃድ ያላገኘ ለውጦችን ማድረግ፣ መጨመር ወይም ማጥፋት፣
27. በDCPS ኔትወርክ ላይ የሚገኙ የመረጃ ስብስብን (data) ለግል ጥቅም ማግኘት ወይም መጠቀም፣
28. በቅድሚያ ከርዕሰ መምህሩ እና የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ የፅሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር፣ ከስርዓተ ትምህርቱ ወይም በትምህርት ቤት-ድጋፍ የማያገኝ ከትምህርት ውጪ እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት የሌላቸው ማንኛውም እንቅስቃሴ ወይም ግንኙነት ማስተዋወቅ ወይም መሳተፍ፣
29. ፈቃድ የሌለው ሶፍትዌር ወይም የሶስተኛ ወገን የአገልግሎት ዘዴን መጫን፣ ዳውንሎድ ማድረግ ወይም መጠቀም፣
30. የተለየ የቴክኖሎጂ፣ አፕሊኬሽን ወይም የDCPS ኔትወርክ ዘዴ ላይ በልዩነት የሚሰራን የሚያገለግል የአጠቃቀም ውልን መጣስ፣
31. የትምህርት ቤትን ወይም የቢሮን ትክክለኛና ስርዓት የያዘ የአሰራር ዘዴን - ለማወክ መስራት፣
32. ሃክ በማድረግ (hacking) (በአለማቀፋዊነት በሕገወጥነት ወይም ካለፈቃድ መግባት መቻል) ወደ DCPS ኔትወርክ በመግባት ያልተፈቀደ መረጃን፣ ወይም የመረጃ የደህንነት ዘዴዎችን ካልሆነም ለማክሸፍ መካፈል፣
33. የማይፈለግ የወሲብ ንክኪ፣ ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ መገላለጥ፣ ወሲብን የሚጋብዙ ምስሎችን ማሰራጨት፣ ወይም ሌላ የወሲብ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፤ ተገቢነት የሌለው የወሲብ ባህሪ ማሳየት፣ ወይም
34. ማንኛውንም በዚህ ፖሊሲ ወይም በሌላ ማንኛውም የDCPS ፖሊሲ ላይ የተከለከለ ነጥብን መጣስ።

ተጠቃሚዎች፣ የDCPS ዲቫይስን ወይም የDCPS ኔትወርክ መግቢያን (log-in) መረጃ፣ ከማንም ሌላ ግለሰብ ጋር ማጋራት የለባቸው። የሌላ ሰውን ከDCPS የተሰጠ ዲቫይስን ወይም ከDCPS የተሰጠ የመግቢያ (log-in) ኔትወርክ መረጃን መጠቀም፣ ፍቃድ-የሌውን ተጠቃሚ ከDCPS የተሰጠ ዲቫይስን ወይም ከDCPS የተሰጠ የመግቢያ (log-in) ኔትወርክ መረጃን እንዲጠቀም ፈቀድ፣ ወይም ከDCPS የተሰጠ ዲቫይስን ወይም ከDCPS የተሰጠ የመግቢያ (log-in) ኔትወርክ መረጃን ለመጠቀም ፈቃድ ከሌለው ጋር እንዲጋራ በማድረግ ማመቻቸት ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መንገድ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

### E. የተማሪ ባህሪ (Conduct) እና የኃላፊነት አጠቃቀም

ሁሉም ተማሪዎችና ወላጆች፣ በየዓመቱ የተማሪ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ በኃላፊነት መጠቀም ስምምነትን (የተማሪ በኃላፊነት የመጠቀም ስምምነት)፣ በአባሪ (Appendix) ላይ የሚገኘውን መፈረም አለባቸው። የተማሪ በኃላፊነት የመጠቀም ስምምነት፣ ተማሪዎች የDCPS ቴክኖሎጂን ወይም የDCPS ኔትወርክን በሚያገኙ ጊዜ፣ የመጠቀሚያ ኃላፊነትንና የተከለከሉ እንቅስቃሴዎችን ዘርዝሯል። ትምህርት ቤቶች፣ የቴክኖሎጂ መግቢያ/መውጫ ሂደቶችን በዝርዝር የሚከተሉ፣ የተለየ ከቴክኖሎጂ ጋር ግንኙነት ያለው የትምህርት ቤት ሠራተኛን የስራ መደብ የሚጠይቅ፣ እና የትምህርት ቤቱ የተለየ ደንቦችን የሚጠቀም፣ የራሱ የሆነ የትምህርት ቤት መለያ የሆነ ስምምነቶችን ተማሪዎች እና ወላጆች እንዲፈርሙ ይጠይቅ ይሆናል።

እነዚህን ደንቦች ለመከተል አለመቻል፣ በDCPS የተማሪ የስነ ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎች ስር የሚጠቀሱ እና ተማሪዎቹ በተሟላ የክፍል

ስራዎች ላይ፣ አማራጭ መንገዶችን በመጠቀም እና ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑ የልዩ ትምህርት ወይም የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች አገልግሎቶችን፣ የDCPS ኔትወርክ ወይም የDCPS ቴክኖሎጂን ማግኘትን ሳይችሉ ለተራዘመ ጊዜ ሊያሳጣቸው ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ መጥፎ ባህሪይ፣ የወንጀለኛ ጥሰትን ሊፈጥሩም ይችሉ ይሆናል።

### F. የግል ሚዲያ የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች

የተማሪዎች የግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶችን መጠቀምን መፍቀድ፣ በDCPS እና የዲሲ ቢሮ የዋናው የቴክኖሎጂ ሹም (D.C. Office of the Chief Technology Officer (OCTO)፣ ፖሊሲዎች መሠረት፣ ርዕሰ መምህሩ በራሳቸው የሚወስኑት ይሆናል። DCPS የተማሪዎችን የግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች የመጠገን እና የደህንነት ጥበቃ የማድረግ ሃላፊነት የሌለበት እና ቢጠፋ ወይም ቢሰረቁም ምንም ኃላፊነት የለበትም። የDCPS ሠራተኞች የግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶቻቸውን ለመጠቀም የጠየቁ ተማሪዎችን የቴክኒካል እርዳታ መስጠት ወይም በDCPS ኔትወርክ ወይም በDCPS ዲቫይሶች ላይ የግል ሚዲያ አካውንታቸውን እንዲያገኙ ለማድረግ አይጠበቅባቸውም። ከዚህ በታች ባለው ክፍል በተገለጸው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣ የDCPS ኔትወርክን በሚጠቀሙ ጊዜ፣ DCPS በግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች ላይ የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን ለማስፈጸም ሲባል እና የDCPS ፖሊሲዎችን ሲጥሱ የተገኙ ዲቫይሶች እንዲወገዱ ያደርጋል።

### G. የተማሪ የግል ሚዲያ አካውንቶች እና የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች ግላዊነት

1. በልዩ ሁኔታ በየትምህርት ቤቱ የተገለጸ፣ የተማሪ የግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይስና ሚዲያ አካውንት ፖሊሲዎች

ርዕሰ መምህራን፣ ስለ ትምህርት ቤቱ የተማሪ የግል የኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ እና ሚዲያ አካውንቶች ፖሊሲ፣ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች በፅሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

2. አጠቃላይ የግል ሚዲያ አካውንቶችና የተማሪ የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች ግላዊነት

በክፍል IV.G.3 የተገለፀው ለየት ያለ ሁኔታ ካልደረሰ በስተቀር፣ DCPS በተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪው ላይ፣ የስነ ስርዓት እርምጃ፣ የማባረር፣ ያለመመዝገብ፣ ለማስገባት መከልከል፣ ወይም በስርዓተ ትምህርት ወይም ከትምህርት ውጪ ለሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዳይካፈል መከልከልን ጨምሮ፣ ተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪው የሚከተሉትን ለማድረግ ፈቃደኛ ስላልሆነ እርምጃ አይወስድም ወይም እርምጃ ለመውሰድ አያስፈራራም:

- የተማሪን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ለመክፈትና ለመጠቀም የሚያገለግል፤ የመጠቀሚያ ስም (username)፣ የሚስጥር ቁልፍ (password) ወይም ሌላ የአካውንት ማረጋገጫን አሳልፎ በመስጠት፣
- የተማሪን የግል ሚዲያ አካውንትን ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን፣ በትምህርት ቤት ተቀማጭ የሆነ ሠራተኛ በተገኘበት፣ በአካውንቱ ወይም በዲቫይሱ ውስጥ ያለውን የመረጃ ስብስብ (data)፣ በትምህርት ቤት ተቀማጭ የሆነው ሠራተኛ እንዲመለከተው ማስቻል፣
- የተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የተማሪውን የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን እንዲመለከቱ ሰዎችን ወደዝርዝሩ መጨመርና እንዲጠቀሙ መፍቀድ፤ ወይም
- ከተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ[7] ጋር ግንኙነት ያለውን ግላዊ አቀማመጦች (privacy settings) መቀየር።

DCPS ወይም የDCPS ሠራተኛ፣ የመጠቀሚያ ስም (username)፣ የሚስጥር ቁልፍ (password) ወይም ሌላ የአካውንት ማረጋገጫ መንገድን፣ በተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ አማካኝነት፤ ሕገወጥነት በሌለው መንገድ ሳያስበው ካገኘ፣ DCPS እና/ወይም የDCPS ሠራተኛ የሚከተለውን ያደርጋል:

- የተማሪውን ወይም የወደፊት ተማሪውን የሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ ተጠቅሞ መረጃዎችን ለማግኘት አይጠቀምም፤
- መረጃዎቹን ከማንም ጋር አለማጋራት፣ እና
- ወዲያውኑ ወይም ልክ እንደተቀበሉ፣[8] መረጃውን ማጥፋት።

በዚህ ክፍል፣ የሚከተሉት DCPSን ምንም አይከለክለውም:

- ስለተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪው፣ በግልጽነት የተቀመጠ መረጃን ማግኘት፣

[7] DC Code § 38-831.04(a).

[8] DC Code § 38-831.04(b).

- ተማሪውን ወይም የወደፊት ተማሪውን ከግል ሚዲያ አካውንቱ ወይም ቴክኖሎጂ ዲቫይስ፣ ተግባራዊ ከሆኑ ሕጎች ወይም የDCPS ፖሊሲዎች፣ ጋር ተገዢ ለመሆን፣ ከፖሊሲ መስፈርቶቹ ጋር አብሮ የሚሄድ ጥያቄን ማቅረብን ተከትሎ፣ የተወሰኑ ይዘቶችን በፍቃደኝነት እንዲያጋራ መጠየቅ፣
- ተማሪውን ወይም የወደፊት ተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንቱ ወይም የቴክኖሎጂ ዲቫይሱን በትምህርት ቤት ሰዓት ወይም በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እያለ እንዳይጠቀም ወይም እንዳይሰራበት መከልከል፣
- የDCPS ኔትወርክ አጠቃቀም ላይ ክትትል ማድረግ፣ ወይም
- ወደ DCPS ኔትወርክ ወይም DCPS ቴክኖሎጂ[9] ያለውን የተማሪ የማግኘት እድል፣ በሙሉ ወይም በከፊል መሻር።

3. በግል ሚዲያ አካውንቶች እና የተማሪ የኤሌክትሮኒክ ዲቫይሶች ግላዊነት ላይ የሚጠበቁባቸው ነገሮች

የDCPS ሠራተኛ የተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ሊፈትሽ ይችላል ወይም ከተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ ውስጥ የመረጃ ስብስብን (data) እንዲያቀርብ ተማሪውን ሊያስገድድ የሚችለው በሚከተሉት ሁለት ሁኔታዎች ይሆናል።

a. የፖሊሲ ጥሰቶች

የDCPS ሠራተኛ የተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ሊፈትሽ ይችላል ወይም ከተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ ውስጥ የመረጃ ስብስብን (data) እንዲያቀርብ ተማሪውን ሊያስገድድ የሚችለው፣ ተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ተጠቅሞ ወይም በመጠቀም፣ የDCPS ፖሊሲን ለመጣስ እገዛ ያደረገን ድርጊት አድርጓል የሚል፣ የDCPS ሠራተኛው ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ ካለው **<u>እና</u>** የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይሱ፣ ለተጠረጠረው ጥሰት[10] ምስክር የሚሆኑ ይዘቶችን ይዟል በሚል ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ ካለ ይሆናል።

ይህን መሰሉን ፍተሻ ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ተማሪው የመረጃ ስብስቡን (data) እንዲያቀርብ ማድረጉ፣ ከመከናወኑ በፊት፣ የDCPS ሠራተኛ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- ፍተሻውን ወይም እንዲያቀርቡ ማድረግን ያነሳሳውን ተገቢነት ያለውን ጥርጣሬን በሰነድነት መመዝገብ፣ እና
- ፍተሻ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ መቅረብ የሚገባውን የመረጃ ስብስብ (data) ወይም ይዘቶች ወይም ተማሪው ተገዶ ማቅረብ[11] የሚገባውን የተጠረጠረውን ጥሰት፤ ተማሪውን እና የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ ያሳውቃል።

ይህን ማስታወቂያ በመጠባበቅ ላይ እያለ፣ የቅድመ-ማስታወቂያ የመያዣ ጊዜው ከ48 ሰዓታት ካልበለጠ እና የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይሱ በተጠበቀ የDCPS ንብረት ውስጥ ከተቀመጠና በቅድመ-ማስታወቂያ የመያዣ ጊዜው[12] ውስጥ ጥቅም ላይ ካልዋለ ብቻ፣ መረጃዎች እንዳይሰረዙ ለመከላከል፣ DCPS የተማሪውን የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ሊወስደው ይችላል።

የፍተሻው ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ማቅረብ ሁኔታው ሊወሰን የሚችለው፣ የመረጃ ስብስቡ (data) ከተገኘበት አካውንት ወይም ከዲቫይስ ወይም ጥሰቱ ተከናውኖበታል ተብሎ ከተጠረጠረበት የዲቫይስ ይዘቶች የማረጋገጫ ምስክሮችን ለማግኘት ሲባል፣ ማንም ሰው ሊያባዛ፣ ሊያጋራ፣ ወይም የመረጃ ስብስቦችን (data) ማስተላለፍ የማይችለው ከዚህ ፍተሻ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ማቅረብ ከተደረገው ጥሰት ጥርጣሬ ጋር ተያያዥነት በሌለው ሁኔታ ፍተሻውን[13] ካነሳሳ ይሆናል።

b. በቅርብ ሊከሰት የሚችል የሕይወት ወይም የደህንነት ስጋት

የDCPS ሠራተኛ፣ በቅርብ ሊከሰት የሚችል የሕይወት ወይም የደህንነት ስጋት[14] ካለ ምላሽ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፤ የተማሪውን የግል የሚዲያ አካውንቱን ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይሱን መፈተሽ ወይም ከተማሪው የግል የሚዲያ አካውንቱ ወይም የግል የቴክኖሎጂ ዲቫይሱ አስገድዶ ሊወስድ ይችላል።

---

[9] DC Code § 38-831.04(e).
[10] DC Code § 38-831.04(c)(1)(A).
[11] DC Code § 38-831.04(c)(1)(B).
[12] DC Code § 38-831.04(d).
[13] DC Code § 38-831.04(c)(1)(C)-(D).
[14] DC Code § 38-831.04(c)(2)(A).

የማንኛውም ፍተሻ ስፋት የሚወሰነው ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የማቅረብ የሚከናወነበው፣ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እና DCPS፣ የፍተሻ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ማቅረብን በተጠየቀበት በ72 ሰዓታት ውስጥ ለተማሪው እና ለተማሪው ወላጆች፣ ፍተሻውን እና መረጃውን ማግኘት[15] ያስፈለገበትን ትክክለኛውን ስጋት በጽሁፍ ዝርዝር መግለጫ ይሰጣል።

## 1. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት አለባቸው።  አፈፃጸሙን ለመደገፍ፣ የሚፈለጉትን እንቅስቃሴዎች እና የጊዜ-አቀማመጥን በዓመታዊ አሰራሩ መሠረት፤ ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣ ከርዕሰ መምህራኖች ይጠበቅባቸዋል። የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና ቦታዎችን መጎብኘት (እንደ አስፈላጊነቱ) - እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት ተጠናክሮ ይካሄዳል። ይህ ማዕቀፍ (framework)፣ ሁላችንም በአንድነት ቀጣይነት ያለው ማሻሻያዎችን እና አለመገዛትን-የሚከላከል ዘዴን እንድንገነባ ያረጋግጥልናል። ቁልፍ የሆኑ መመሪያና እርዳታን ከጥያቄዎች፣ ከስልጠና ወይም ከማስፈጸም ጋር ለማግኘት ከፈለጉ፣ እባክዎችን dcps.dc.gov ይጎብኙ።

DCPS እያንዳንዱን ተማሪ በፍህታዊነት፣ በላቀ ሁኔታ፣ በግልጽነት፣ እና በተጠያቂነት ለማገልገል ቁርጠኝነቱን ያሳያይል። ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ጥሰቶች ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ነገሮች ሪፖርት ለማድረግ፣ ይህን  ትዕዛዝ መስጫ፣ የሃቀኝነት ሹም ቢሮን ለማነጋገር፤ የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን[16] በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@dc.gov. ኢሜል መላክ።

## 2. አባሪ (APPENDIX)

የሚቀጥለውን ገጽ ይመልከቱ: የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም ስምምነት

[15] DC Code § 38-831.04(c)(2)(B)-(C).
[16] *Available at* https://dcps.dc.gov/page/office-integrity.

# የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም ስምምነት
# የትምህርት ዓመት __________

ሁሉም የDCPS ተማሪዎች፣ የDCPS ኮምፒውተሮችን እና ሌሎች የDCPS ቴክኖሎጂ (የDCPS መሣሪያዎች "DCPS devices") እና የDCPS አውታረ መረብ (network)ን በኃላፊነት፣ በአስተማሪዎች እና የDCPS ሠራተኞች መመሪያ መሠረት በሚከተለው ሁኔታ መጠቀም አለባቸው:

**A. የDCPSን መሣሪያዎች (devices) በጥሩ ሁኔታ የመጠበቅ ኃላፊነት አለብኝ።**

- የDCPS ዲቫይሶችን በማመስገን እና በማክበር፣ እንዳይወድቅ ጥንቃቄ በማድረግ እንከባከባለሁ።
- የDCPS ዲቫይሶቼን፣ ስለመፈተሽ እና ስለመመለስ፣ የትምህርት ቤቱን ደንቦች እከተላለሁ።
- በDCPS ዲቫይሶቼ አቅራቢያ፣ አልበላም ወይም አልጠጣም።
- በDCPS ዲቫይሶቼ ላይ አልፅፍም፣ ስዕል አልስልም፣ ወይም ተለጣፊ ነገሮችን (stickers) አልለጥፍበትም።
- ከቦታ ወደ ቦታ ስንቀሳቀስ፣ የDCPS ዲቫይሶቼን የመመልከቻ መስኮት (screen) በመዝጋት ደህንነቱን እንከባከባለሁ።
- በDCPS ዲቫይሶቼ የመመልከቻ መስኮት (screen) ላይ ጉዳት እንዳይደርስ፣ አልደገፍም ወይም ማንኛውም ከባድ ነገር አላስቀምጥም።
- ተጨማሪ ዕቃዎች (accessories) እንደ፣ የጆሮማዳመጫ (headphones)፣ ስታይለስ እስክሪብቶ (stylus pens)፣ እና ኪቦርዶች (keyboards) አላበላሽም።
- የDCPS ዲቫይሴ የተበላሸ ከሆነ ወይም በትክክል የማይሰራ ከሆነ፣ ወዲያውኑ ለአስተማሪ ወይም ለሠራተኛ አባል ሪፖርት አደርጋለሁ።
- የDCPS ዲቫይሴን ወይም የDCPS ኔትወርክ መግቢያዬን (log-in) መረጃ፣ ከማንም-ሌላ ግለሰብ ጋር አላጋራም።

**B. ለDCPS አካውንቶቼ ኃላፊነት አለብኝ።**

- የቅድመ-ልጅነት ተማሪ ካልሆንኩ በስተቀር፣ ወይም የሆነ-እክል ምክንያት የጉዳተኛ ተማሪ በመሆኔ ምክንያት የወላጆች ወይም የሠራተኛ እርዳታን በአካውንቴ አጠቃቀም ላይ የሚያስፈልገኝ ካልሆነ በስተቀር፤ የመጠቀሚያ ስሜን (username) ወይም ሚስጢራዊ መግቢያዬን (password) ከማንም ጋር አላጋራም።
- ስራዬን ስጨርስ፣ ሁሉንም ስራዬን እንዲቀመጥ (save) አድርጌ፣ እና ከአካውንቴ እና ፕሮግራሞቼ (log out በማድረግ) እወጣለሁ።
- በእኔ አካውንቶች በኩል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ሁሉ፣ እኔ በኃላፊነት እጠየቃለሁ።
- ሌላ ሰው አካውንቴን እንደሚጠቀም ከገመትኩኝ ወይም ካወኩኝ፣ ለአስተማሪውዬ እነግራለሁ።

**C. DCPSን አውታረ መረብ (network) በደህንነት የተጠበቀ እንዲሆን ለመርዳት ኃላፊነት አለብኝ።**

- ከአስተማሪዬ ፈቃድ ውጪ፤ ድህረ-ገጾችን፣ ሶፍትዌሮችን፣ አፖችን (apps)፣ የብራውሰር ተቀጥያዎችን (browser extensions)፣ ወይም ሚዲያን፣ ወይም የሙዚቃ እና የቪዲዮ ፋይሎችን ጨምሮ - ማንኛውንም የፋይል ዓይነቶችን እንዲንቀሳቀሱ (run)፣ ዳውንሎች (download)፣ መጫን (install) አላደርግም።
- የኢንተርኔት ይዘቱን፣ ማጣሪያው እንዲያልፈው ለማድረግ ሲባል፣ የደህንነት ጥበቃውን ወይም የኢንተርኔት ይዘት ማጣሪያውን የቅንብር አቀማመጥ (settings)፣ ወይም ከኔትወርክ ጋር የሚገኘውን ማንኛውንም ኢንተርፌስ (interfere) ለመቀየር በመሞከር ሳቢያ፣ አፕሊኬሽኖችን (applications) ወይም የብራውሰሮችን ፕላግ-ኢን (browser plug-ins) ዳውንሎድ አላደርግም ወይም አልጭንም።
- በአስተማሪዬ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደልኝ በስተቀር፣ በዲቫይሴ ውስጥ፣ የUSB drives (ፍላሽ ድራይቭ (flash drives)፣ ታም ድራይቭ (thumb drives)፣ ጃምፕ ድራይቭ (jump drive)፣ ዳታ ስቲክ (data sticks)፣ ወይም በሌሎች ስሞችም የሚታወቁትን) አልጨምርም።

**D. የDCPSን አውታረ መረብ (network) አጠቃቀሜ ላይ ኃላፊነት አለብኝ።**

- የጥላቻን የሚያንፀባርቁ፣ የሴሰኛነት፣ የብልግና ወይም ወሲባዊነትን በይፋ የሚሳዩ ነገሮችን፣ መፈለግ (search)፣ ከስር ማውጣት (retrieve)፣ ማስቀመጥ (save)፣ ማሰራጨት ወይም እንዲታዩ አላደርግም።
- ለትምህርት ቤት የቤት-ሥራነት አስፈልጎ፣ ከአስተማሪ ፈቃድ ካላገኘውሁ በስተቀር፣ ስለ ጦር-መሳሪያዎች ወይም ሕገወጥ ዕፆች፤ ምስሎችን ወይም መረጃዎችን መፈለግ (search for)፣ ከስር ማውጣት (retrieve)፣ ማስቀመጥ (save)፣ ማሰራጨት ወይም እንዲታዩ አላደርግም።
- የወንበዴ (gang) ወይም የቡድን (crew) እንቅስቃሴ፣ በሌላ ሰው አካላዊ ጉዳት ለማድረስ በማስፈራሪያነት፣ ወይም ኮምፒውተርን ሃክ ማድረግ (computer hacking) ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ማንኛውም ሕገወጥ ወይም የወንጀል እንቅስቃሴ ላይ ለመሳተፍ የDCPS ኔትወርክን አልጠቀምም።
- በአስተማሪ ወይም የሠራተኛ አባል ክትትል እየተደረገበት፣ እና ለትምህርት ስራ፣ ከትምህርት ቤቱ ትምህርት ዓይነት ጋር ግንኙነት ከሌለው በስተቀር የኦንላይን ጨዋታዎችን (online games) አልከፍትም።
- የማህበራዊ ሚዲያዎችን (social media)፣ የመልዕክት አፖችን (messaging apps)፣ እና የቡድን መነጋገሪያዎችን (group chats)፣ ከትምህርት ቤት ስራዎች ጋር ግንኙነት ከሌላቸው እና ከአስተማሪው ፍቃድ ካልሰጠ በስተቀር አልከፍትም። ይህም፣ የFacebook፣ Twitter፣ Instagram፣ TikTok፣ Snapchat፣ WhatsApp፣ Kik፣ Telegram፣ እና Tumblr ጨምሮ፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰን ይሆናል።

**E. በኦንላይን የምጠቀመው ቋንቋ እና ሌሎችን እንዴት እንደምንከባከብ፣ እኔ ኃላፊነት አለብኝ።**

- ወሲባዊነትን በይፋ የሚገልጹ፣ የወሲብ ክንውን (pornographic)፣ ፀያፍ ወይም ወራዳ የአነጋገር ቋንቋን የሚፈጥሩ ማንኛውንም ምስሎችን፣ ድምፆችን፣ ወይም መልዕክቶችን፣ ወይም ደግሞ ሌሎችን አልፈጥርም፣ አለጥፍም፣ አላሰራጭም።

- ሌሎች ሰዎች ላይ፣ የጥላቻ፣ ወከባን የሚፈጥሩ፣ አዋራጅ ወይም አድሎዓዊ መልዕክቶችን በመላክ፣ ማጋራት ወይም በመለጠፍ፤ አላንጓጥጥም፣ ወከባ አልፈጥርም፣ ዛቻ ወይም ማስፈራራት አላደርግም።

**F. ኦንላይን በምጠቀም ጊዜ ሐቀኛ የመሆን ኃላፊነት አለብኝ።**

- ለማጭበርበር በማሰብ፣ አንድ ሌላ ሰውን መስዬ በኦንላይን አልቀርብም። ይህም ማለት፣ እኔ ያን ሰው እንደሆንኩ ሌሎችን ለማሳመን በሚል፣ የሌላ ሰውን አካውንት፣ ስም ወይም ፎተግራፍ ተጠቅሜ፣ ኢሜል አልክም፣ አካውንት አልፈጥርም ወይም ማንኛውንም ቃላት፣ ምስል ወይም ድምፆችን አልለጥፍም።
- የሌላ ሰው የመግቢያ ስም (login name) እና የሚስጥር መግቢያ ኮድ (password) አልጠቀምም።

**G. በኦንላይ የሌሎች ሰዎችን ንብረት ለማክበር ኃላፊነት አለብኝ።**

- የሌላ ሰው ስራን በተገቢው ሁኔታ የተገኘበትን ሳልጠቅስ በመጠቀም አላጭበረብርም።
- ከባለቤቱ ፈቃድ ሳላገኝ፣ የሌላ ሰውን ስራዎች (ለምሳሌ፣ የቅጂ መብት ያላቸው)፣ መጽሐፍትን፣ ሙዚቃ እና ፊልሞችን ጨምሮ ዳውንሎድ አላደርግም።
- ካለፈቃድ የአስተማሪዎችን ወይም በሌሎች ተማሪዎች ባለቤትነት የሚገኙ ፋይሎችን አላነብም፣ አላስተካክልም፣ ወይም አላጠፋም።
- የሌላ ሰውን ስራ በኮምፒውተር መስኮት ብመለከት፣ ወይም ሌላ ተማሪ በኮምፒተሩ ሲጠቀም ባይ፣ አስተማሪን ወይም የሠራተኛ አባል ለሆነ ሰው አስታውቃለሁ፤ ኮምፒውተሩንም ለመጠቀም ሌላው ተማሪ ከአካውንቱ እስኪወጣ (logged off) እጠብቃለሁ።

**H. በማንኛውም ጊዜ የDCPS ዲቫይስን ወይም የDCPS ኔትወርክን ተጠቅሜ በኦንላይን የምለጥፈው ነገር ሁሉ የትምህርት ቤቱን ደንቦች ተከትዬ ለመሆኑ ኃላፊነት አለብኝ።**

- ማንኛውንም ነገሮች በትምህርት ቤቱ ድህረ-ገጽ፣ ዊኪ (wiki)፣ ብሎግ (blog)፣ ፖድካስት (podcast)፣ ማህበራዊ ሚዲያ አካውንት ወይም የቡድን ውይይት ላይ፣ ከአስተማሪ ወይም የሰራተኛ አባል ፈቃድ ውጪ አልለጥፍም።
- የራሴን ፎተግራፍ ወይም ቪዲዮዎችን፣ ስሜን ወይም ሌላ ማንኛውምን የግል መገለጫዎቼን ጨምሮ፣ ማንኛውንም ፎተግራፎች ወይም የድምጽ ቅጂዎችን አለጥፍም።
- ካለ ፈቃድ የማንም ፎተግራፎች፣ በድምፅ የተቀረጹ ነገሮችን፣ ወይም ቪዲዮዎችን አላዘጋጅም ወይም አለጥፍም።

**I. የDCPS ዲቫይሴን፣ ፋይሎቼን እና አካውንቶቼን፤ DCPS ሊከፍትና ሊመለከት እንደሚችል ተገንዝቤአለሁ።**

- እንደአስፈላጊነቱ የDCPS ሠራተኛ ሁሉንም በDCPS ኔትወርክ (network) ላይ የሚገኙ ወይም በDCPS ዲቫይሶች ላይ እንዲቀመጥ የተደረጉ ፋይሎችን በማንኛውም ጊዜ መፈተሽ እና ማግኘት እንደሚችሉ ተረድቻለሁ።
- እንደየአስፈላጊነቱ፣ የDCPS ሠራተኛ በግል የሚዲያ አካውንቴ ወይም መሳሪያን ሊፈትሽ እንደሚችል፣ ወይም ከግል ሚዲያ አካውንት ወይም መሳሪያው ውስጥ የመረጃ ስብስብ በሚከተሉት ምክንያት እንዳቀርብ ልጠየቅ እንደምችል ተረድቻለሁ:
    - የDCPSን ፖሊሲን (ለምሳሌ፣ ማንጓጠጥን የመከላከል ፖሊሲ) በሚጥስ ሁኔታ አካውንቴን ወይም መሳሪያውን እየተጠቀምኩ ወይም ስጠቀም እንደነበረ፣ የDCPS ሠራተኛ ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ ካለው ወይም አካውንቴ ወይም መሳሪያው የተጠረጠውን ጥሰት ማስረጃ አለው ተብሎ ከተገመተ፤ ወይም
    - በቅርብ ጊዜ ሊከሰት የሚችል የሕይወት ወይም የደህንነት ማስፈራራት ላይ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

# የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም የስምምነት ማረጋገጫ ቅፅ

**ተማሪዎች:**

**የተማሪ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስምምነትን አንቤአለሁ፤ ወይም ሌላ ሰው አንብቦልኝ እና ዝርዝሩን አስረድቶኛል። የDCPS ዲቫይሶችን እና የDCPS ኔትዎርክን በስምምነቱ ዝርዝር ላይ በተጠቀሰው ሕግጋት መሠረት በኃላፊነት ለመጠቀም ተስማምቻለችሁ። እነዚህን ሕግጋት ካልተከተልኩ፣ ከDCMR Chapter 25 policy ጋር አብረው የሚሄዱትን፣ በDCPS የስነ ስርዓት ሕጎችና ፖሊሲዎች ስር ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ የምጋፈጥ መሆኔንና፣ የDCPS ዲቫይሶችን እና የDCPS ኔትወርክ የማግኘት ገደብ ሊደረግብኝ እንደሚችል ተረድቻለሁ። የDCPS ዲቫይስን ወይም የDCPS ኔትወርክን፤ ለማንጓጠጥ፣ ለማስፈራራት፣ ለዛቻ፣ ለማዋከብ፣ ወይም ሌላ ሰው ላይ ጥላቻን ለማንፀባረቅ ጥቅም ላይ ሲውል ብመለከት ወይም ሌላ ሰው እንደሚጠቀምበት ከተገነዘብኩኝ፣ ይህን ለአስተማሪ ወይም የሠራተኛ-አባል ሪፖርት እንዳደርግ እንደምበረታታ ተገንዝቤአለሁ። ያቀረብኩት ሪፖርት በሚስጥር እንደሚያዝ፣ እና ሪፖርት በማድረጌ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውም የበቀል ጥቃትን፣ DCPS በትዕግስት እንደማያልፈው ተገንዝቤአለሁ።**

1. በውሰት የተሰጠኝ የDCPS ዲቫይስ፣ የDCPS ንብረት የሆነና የትምህርት አሰጣጥን እና ለስርዓተ ትምህርት ማካሄጃነት ብቻ ለመጠቀም፤ እና በDCPS የተማሪና ሠራተኛ ቴክኖሎጂና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ መጠቀሚያ ፖሊሲ መሠረት፣ በተውሶ የተሰጠኝ ነው። በ2016 የተማሪዎች የዲጂታል የግል ደህንነት ጥበቃ ድንጋጌ (Protecting Students Digital Privacy Act of 2016) በመከተል፣ DCPS፣ የላፕቶፑን (the laptop) የመረጃ ስብስቦችን (data) የሚሰበስብ እና አጠቃቀሙን ይቆጣጠራል።
2. ላፕቶፑ (laptop) በተውሶ ላይ እንዳለ፣ በቸልተኝነት ወይም ሆን-ብዬ ባደረኩት እርምጃዎች ከሚደርሱ ብልሽቶች ጋር በተያያዥነት ማንኛውንም የማስጠገኛ ክፍያዎች ላይ ኃላፊነት አለብኝ።
3. በDCPS በሚጠየቅበት ጊዜ፣ ላፕቶፕ (laptop) መመለስ አለበት። ይህን ዲቫይስ እንድመልስ በDCPS በምጠየቅ ጊዜ ካልመለስኩ፣ ክፍያውን ቤተሰቦቼ እንዲከፍሉ ሊያደርጋቸው ይችላል።

የዲቫይሱ ዓይነት/የDCPS ንብረት መለያ (Tag) ቁጥር ______________________________

የተማሪ ስም (ይፃፍ)______________________________

የተማሪ ፊርማ______________________________ቀን______________

የDCPS ተወካይ ስም (ይፃፍ)______________________________

የDCPS ተወካይ ፊርማ______________________________ቀን______________

## ወላጆች/አሳዳጊዎች:

**የተማሪ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስምምነቱን አንብቤና ከተማሪዬ ጋር ተወያይቼበት፣ ወይም አዋቂ ተማሪ ከሆኑ ደግሞ፣ የተማሪ ቴክኖሎጂ መጠቀሚያ ስምምነቱን አንብቤዋለሁ ወይም ሌላ ሰው ለእኔ አንብቦልኛል። ተማሪዬ እነዚህን ሕግጋት መከተል ካልቻሉ፣ Chapter 25ን ጨምሮ፣ በDCPS የስነ ስርዓት ሕጎችና ፖሊሲዎች ስር ሊያስከትል የሚችለውን መዘዝ የሚጋፈጡና፣ የDCPS ዲቫይሶችን እና የDCPS ኔትወርክ የማግኘት ገደብ ሊደረግባቸው እንደሚችል ተረድቻለሁ።**

**ለእኔ/ለተማሪዬ ለተሰጠው የDCPS ቴክኖሎጂን በተመለከተ፣ በሚከተሉት ላይ እውቅናን፣ እና ስምምነቴንም እገልፃለሁ:**

1. ይህ ዲቫይስ በDCPS ባለቤትነት የሆነ እና ለእኔ/ለተማሪዬ በተውሶ የትምህርት አሰጣጥን እና የቀለም ትምህርትን ዓላማ በማድረግ ብቻ የተሰጠ፣ እና በDCPS ተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ መጠቀሚያ ፖሊሲን በተከተለ ለመጠቀም የተሰጠ ነው። DCPS፤ ከ'2016ቱ፣ የProtecting Students Digital Privacy Act' ተገዢነት መሠረት፣ የመረጃ-ስብስብ (data) የሚሰበስብ እና የዲቫይሱን አጠቃቀም የሚቆጣጠር ይሆናል።
2. እኔ/ተማሪዬ ከጠፋብን እና/ወይም፣ እኔ/ተማሪዬ ሆን ብለን ወይም በግዴለሽነት ዲቫይሱን እንዳበላሸነው DCPS ከወሰነ፤ በDCPS ተገቢ የሆነ የስነ-ምግባት መቅጫ እኔ/ተማሪዬ ልንጋለጥ እንደምንችል፣ እና እኔም ከDCPS ጋር በመገናኘት የመጥፋቱ/መበላሸቱን ምክንያት በማስረዳት፣ እና ዲቫይሱን በኃላፊነት ለመጠበቅ ተማራጭ የሆነውን ልምዶችን ለመወያየት እገናኛለሁ።

3. ዲቫይሱ በDCPS በሚጠየቅ ጊዜ መመለስ እንዳለበት፤ በተጨማሪም ተረድቻለሁ። በተጠየቀ-ጊዜ ዲቫይሱን መመለስ ካልቻኩ፣ ዲቫይሱ በሪሞት (remotely) እንዳይሠራ ሊደረግ ይችላል።

የወላጅ/አሳዳጊ ስም (ይፃፍ) ______________________________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ______________________________ቀን______________